# አገር የማዳን ጥሪ ከወጣቶች ለወጣቶች

በእኛ በኢትዮጵያውያኖችም ታሪክ ሆነ በአለም ታሪክ ውስጥ ወጣቶች በአገራቸው የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ያላቸው ሚና እጅግ ከፍተኛ መሆኑ አሌ የማይባል ነው። ርቀን ሳንሄድ ባላፉት ሰላሳና አርባ አመታት በአገራችንና በሕብረተሳባቸን ለውጥ ለማምጣት ወጣቶች ያደረጉትና የከፈሉት መስዋእትነት የትየለሌ ነው። እንዲያውም ለራሳችን ጀግኖች ክብር እንስጥ ካልን ባለፉት ሰላሳና አርባ አመታት በአለም ዙሪያ ከተደረጉት የወጣት እንቅስቃሴዎች አንፃር የኢትዮጵያ ወጣቶች እንቅስቃሴ በጠንካራነታቸውና በይዘታቸውም ታዋቂና ተጠቃሾች ከነበሩት አንዱ እ ንደነበረ ሊካድ የማይችል ነው።ይህ ሃቅ በወጣቶች አኩሪ ታሪክ አምድ ውስጥ የተመዘገበ እውነታ ነው። አሁንም አገራችን ባለችበት የከፋ ወቅት ወጣቶች የምንከፍለው መስዋእትነት በቀላሉ የሚመዘን አይደለም። አንድ አገር እንደ አገር ቀጣይነቱን ለማረጋገጥም ሆነ የአንድ አገር ሕዝብ እንደ አንድ አገር ሕዝብ ማሰቡንና በአንድ ላይ ተስማምቶና ተቻችሎ መኖሩን ለማስጨበጥ ወጣት ዜጎች ለአገራቸውና ለህዝባቸው ሃላፊነት እንዲሰማቸው ማድረግ የግድ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በሃገራችን ፓለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሂደት ውስጥ ንቁ የሆነ ተሳትፎ እንዲኖረን ተሰብስበን  መመካከርና መደራጀት ይገባል ከሚልም በቅርቡ ዋሽንገተን ዲሲ የሚደረገውን የሰሜን አሜሪካ የእግር ኳስ ዝግጅት በማስታከክ ለወጣቶች መወያያ የሚሆን  ስብሰባ አዘጋጅተናል። ይህ ስብሰባ እኛ ወጣቶች የአገራችንን አስከፊ የድህነትና የበሽታና የፖለቲካዊ ገፅታን በመጠኑም ቢሆን የምንወያይበት ሲሆን፤ ወደፊትም በአለም አቀፍ ዙሪያ እንዴት መሰባሰብ እንደምንችል የምንነጋገርበት ይሆናል። የስብሰባው ፕሮግራም ወጣት ተናጋሪዎች፣ ባለፈው ዘመኖች ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ስላደረጉት ተጋድሎ አጭር ገለፃና ከአዛውንቶችም ምክርና መልእክት ያካተተ ይሆናል። ወጣቶች ይህንን ስብሰባ በመሳተፍ ወደፊት ለአገራችን ኢትዮጵያም ሆነ ለሕዝባችን ዘላቂ ጥብቅና በጋራ የምንቆምበትን መሰረት እንጣል።

ቀን፡ July 3, 2008
ሰአት፡ 1፡00 p.m.
ቦታ: St. George Ball Room and Conference Center
4335 16th street. North West
Washington D.C. 20011

እኛ ወጣቶች ላገራችን ብሩህ ተስፋዎች ነን!

ይህ ስብሰባ ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮያዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ተባባሪነት የተዘጋጀ ነው።

የበለጠ ለመረዳት የስልክና የፋክስ ቁጥራችን 301-578-4466